አዋጅ ቁጥር..../2015

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የህግ ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የህግ ትብብር ስምምነት እ.ኤ.አ. ግንቦት 10 ቀን 2022 በአንካራ የተፈረመ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (12) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የህግ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር..../2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል እ.ኤ.አ. ግንቦት ሜይ 10 ቀን 2022 በአንካራ የተፈረመው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የህግ ትብብር ስምምነት ፀድቋል፡፡

3. **የኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊነት**

የኢፌዴሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

4. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ..... ቀን .......... ዓ.ም.

**ሳህለወርቅ ዘዉዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**